# ሰነድ ሙዓለ ንዋይን ለህዝብ ማቅረብ

## የቁጥጥር ማዕቀፍ እና የኢንቨስተሮች ጥበቃ ዘዴዎች አጠቃላይ ትንተና

በባለፈው ጽሁፍ የሰነደ ሙዓለ ንዋይን ለህዝብ ማቅረብ እና ግብይት መመሪያ አጠቃላይ ይዘት እና የተወሰኑ ክፍሎችን በዝርዝር አይተናል። በዚህ ክፍል ቀሪዎቹን የመመሪያውን ይዘት እንደሚከተለው እንዳስሳለን።

አውጪው የምስረታ ሂደቱን ያጠናቀቀ ነገር ግን ከሦስት ዓመት ያነሰ እድሜ ያለው ከሆነ እና ኦዲት የተደረገ የሦስት ዓመት የፋይናንስ መግለጫ ማቅረብ የማይችል ከሆነ በምትኩ ከተመሠረተበት ቀን ጀምሮ ደንበኛ ሳቢ መግለጫው እስከታተመበት የመጨረሻው ቀን ድረስ ያለውን ጊዜ የሚሸፍን የፋይናንስ ኦዲት መረጃ ማቅረብ ይጠበቅበታል። በተጨማሪ አውጪው አጠቃላይ የንግድ ሥራ እቅዱን ጨምሮ ስትራቴጂካዊ ዓላማዎቹን፣ አዳዲስ ምርቶች/አገልግሎቶች በማስተዋወቅ ንግዱን ለማሳደግ ያለውን እቅድ እና የገቢ ማስገኛ ዕቅዶቹን፣ ከሥራው ዕቅድ ጀርባ ያሉ ቁልፍ እሳቤዎቹን፣ መነሻዎች እና የተጽዕኖ ግምገማዎቹን ማካተት አለበት።

ባለሥልጣኑ እንደዚህ አይነት አውጪን ምስረታ ላይ እንደሚገኝ ኩባንያ ሊቆጥረው እንደሚችል ይህ ደግሞ ለምሳሌ መጀመሪያ የካፒታሉን 10% በግል ሽያጭ መሰብሰብ እና የህግ ማስከበር አማካሪ መሾም የሚሉትን ተጨማሪ መስፈርቶች በአንቀጽ 13 መሠረት የማሟላት ግዴታ ያስከትላል።

ሌላው ባለሥልጣኑ የቀረበለትን የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ዋጋ ምዘና ሪፖርት እውነተኝነት እና ትክክለኛነት የሚጠራጠር ከሆነ፣ ባለሥልጣኑ በሌላ የግብይት አማካሪ ሁለተኛ ግመታ እንዲደረግ እና ሪፖርት እንዲቀርብለት ሊጠይቅ ይችላል። አውጪው ወይም አቅራቢው ሁሉንም ወጪዎች ይሸፍናል። የግመታ ሪፖርቱ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮቹ የሚቀርቡበትን ዋጋ የሚወስን በመሆኑ አውጪው ማጭበርበር፣ ከመጠን በላይ ዋጋ መስጠት ወይም ደካማ የዋጋ ግኝት ዘዴ የተጠቀመ መሆኑን ባለሥልጣኑ ከጠረጠረ፣ በገለልተኛ ወገን እንዲጣራ ሊያስገድድ ይችላል። ይህ ለኢንቨስተሮች ጥበቃ ዋንኛ እርምጃ ሆኖ ያገለግላል።

ሌላው የምዝገባ ሰነድ የደንበኛ ሳቢ መግለጫ አካል የሆነው ገለልተኛ የውጪ የሕግ አስተያየት ሲሆን የሚዘጋጀውም ፈቃድ ባለው ጠበቃ እና የህግ አማካሪ ነው። ለአውጪው የሚዘጋጀው እና ለባለሥልጣኑ የሚቀርበው ገለልተኛ የውጭ የሕግ አስተያየት አውጪው በአግባቡ የተቋቋመና ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ለማውጣት የተፈቀደለት መሆኑን፣ የአውጪው ካፒታል (እና ማንኛውም የቀረቡ ለውጦች) ከሚመለከታቸው ህጎች ጋር የሚጣጣም እና ሁሉንም አስፈላጊ ፈቃዶች ያገኘ መሆኑን፣ ለአውጪው ንግድ የሚያስፈልጉ ሁሉም ፈቃዶች (በደንበኛ ሳቢ መግለጫው ውስጥ በተገለጸው መልኩ) በአግባቡ የተገኙ መሆኑን፣ ለአውጪው ንግድ የሚያስፈልጉ ሁሉም ይሁንታዎች (በደንበኛ ሳቢ መግለጫው ውስጥ በተገለጸው መልኩ) በአግባቡ የተገኙ መሆኑን፣ በደንበኛ ሳቢ መግለጫ ውስጥ የተገለጹት የአውጪው ዋናዋና ንብረቶች ባለቤትነት ትክክል መሆኑን፣ የአውጪው ከውክልና ሻጩ፣ ከግብይት አማካሪው እና ከሌሎች ባለሙያዎች ጋር ያደረገውን ስምምነት ጨምሮ ሌሎች ወሳኝ ውሎች፣ እና ማናቸውም አውጪውን ወይም የሚያወጣውን ሰነደ ሙዓለ ንዋይ ህጋዊ ቁመና የሚመለከቱ ወሳኝ መረጃዎች ማካተት አለበት።

የህግ ባለሙያው የሚሰጠው አስተያየት የህግ አደጋ (Legal Risk) አካባቢዎችን ዝርዝር የሚሸፍን መሆን አለበት። አስተያየቱ የሚጠቅመው ለባለሥልጣኑም ሆነ ለሌላው አካል አውጪው ህጋዊ መሆኑን፣ ፈቃድ ያለው መሆኑን እና ባለቤት ነኝ የሚለውን ንብረት የያዘ መሆኑን ለማረጋገጥ ስለሚረዳ ነው። ባለሥልጣኑ መረጃው ትክክለኛ፣ በቂ፣ ግልጽ፣ ሁሉንአቀፍ፣ ምክንያታዊ የሆነ እና ወቅታዊ መሆኑን ለማረጋገጥ የምዝገባ መግለጫውን ይገመግማል።

ሆኖም ባለሥልጣኑ የሰነደ ሙዓለ ንዋዩን ግብይት አዋጪነት የማይገመግም መሆኑ በመመሪያው ተመልክቷል።

ይህ ማለት አንድ አውጪ ለምዝገባ ያቀረበው ሰነድ ከትርፍ አንጻር አዋጪ መሆን አለመሆኑን በተመለከተ ባለሥልጣኑ ግምገማም ሆነ አስተያየት አይሰጥበትም። በተጨማሪ ባለሥልጣኑ የአውጪውን ሰነዶች ገምግሞ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮቹን መመዝገቡ የአውጪውን ሰነዶች ሙሉ ወይም ትክክለኛ መሆኑን ዋስትና አይሆንም። በዚህ ረገድ ለአውጪው ሰነዶች ትክክለኝነት ሙሉ ኃላፊነት የሚቆየው ከአውጪው እና ፋይሎቹን ባዘጋጁት ባለሙያዎች ላይ ነው። በተጨማሪም የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ምዝገባ ሰነዶቹን ሌሎች እንቨስተሮች እንዲገዙ ወይም እንዲሸጡ እንደ ምክር ወይም ስለተመዘገበው መረጃ ትክክለኝነት ማረጋገጫ ተደርጎ ሊወሰድ አይገባም። በዚህ ረገድ የምዝገባው ዋና አለማ ከአውጪው ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች መግዛት የሚፈልጉ ማናቸውም ኢንቨስተሮች ከመግዛታቸው በፊት ስለአውጪው የተመዘገበውን ደንበኛ ሳቢ መግለጫ በማንበብ የራሳቸውን ውሳኔ እንዲደርሱ ማስቻል ነው።

ባለሥልጣኑ አውጪው ባቀረበው የደንበኛ ሳቢ መግለጫ አስተያየቶችን ሰጥቶ ከመለሰ አውጪው ሁለተኛ ረቂቅ ሲያቀርብ በባለሥልጣኑ በመጀመሪያ ረቂቁ ላይ የተሰጡ አስተያየቶችን መሰረት በማድረግ የተደረጉትን ለውጦች ሁሉ በሰነዱ ላይ ማሳየት፣እያንዳንዱ አስተያየት በሁለተኛው ረቂቅ ላይ በምን መልኩ እንደተስተካከለ የተለየ የጽሑፍ ማብራሪያ ማቅረብ እና ለውጦቹ ምልክት ያልተደረገበት ንጹህ ቅጂ ማቅረብ አለበት።

# ሰነድ ሙዓለ ንዋይን ለህዝብ ማቅረብ

## የቁጥጥር ማዕቀፍ እና የኢንቨስተሮች ጥበቃ ዘዴዎች አጠቃላይ ትንተና

ይህ የቁጥጥር ሥርዓት የአውጪውን ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች የምዝገባ መስፈርቶች ለመረዳት ወሳኝ ነው። ነገር ግን የአውጪው የምዝገባ መግለጫ ተመዘገበ ማለት ሰነደ ሙዓለ ንዋዮቹ ተመዘገቡ ማለት እንጂ የአውጪውን ሰነደ ሙዓለ ንዋይ መግዛትም ሆነ መሸጥ አዋጭ ነው ወይም አይደለም ማለት አለመሆኑን ወይም ኢንቨስትመንቱ ጥሩ መሆኑን "ያረጋግጣል" ማለት አለመሆኑን መረዳት ያስፈልጋል።

የአውጪው ምዝገባ ማለት አውጪው ይፋ ማድረግ የሚገባቸውን ሁሉንም ሰነዶች በመመሪያው መሰረት በግልጽነት እና ሙሉነት መስፈርቶችን በማሟላት ሲያቀርብ ባለሥልጣኑ ይህንን ገምግሞ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮቹን የሚመዘግብበት እና የምዝገባ መግለጫውን የሚያጸድቅበት ሥርዓት ነው።

በመመሪያው መሰረት የቀረበ የምዝገባ ማመልከቻ ለመጀመሪያ ዙር የሕዝብ ሽያጭ ከሆነ እስከ ሰላሳ የሥራ ቀናት ድረስ ካልሆነ ደግሞ እስከ ሃያ የሥራ ቀናት ድረስ በባለሥልጣኑ መታየት ያለበት ሲሆን በቀረበው ሰነድ መስተካከል ያለበት ስህተት ወይም ያልተሟላ ሰነድ ሲኖር የጊዜ ገደቡ እንደገና መቁጠር እንደሚጀምር ተመልክቶ ይገኛል። በሌላ አነጋገር አውጪው ለባለሥልጣኑ ያቀረበው ሰነድ ክለሳ ወይም ማብራሪያ ወይም እርማት የሚያስፈልጋቸው አስተያየቶችን ሲሆኑ የጊዜ ሰሌዳው እንደገና መቁጠር ይጀመራል። ይሁን እንጂ ባለሥልጣኑ በእነዚህ የጊዜ ገደቦች ውስጥ የአውጪውን ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን አለመመዝገቡ ወይም የምዝገባ መግለጫውን አለማጽደቁ ወይም ማዘግየቱ እንደተመዘገበ አያስቆጥርም።

ባለሥልጣኑ በምዝገባ መግለጫው ውስጥ የተካተቱት የደንበኛ ሳቢ መግለጫ ወይም የግዥ ጥያቄ ማቅረቢያ ሰነዶች የተሟሉ፣ ትክክለኛ፣ በቂ እና ግልጽ፣ ሁሉንአቀፍ፣ ምክንያታዊ የሆነ እና ወቅታዊ ሆኖ ካገኘው እንዲሁም ምዝገባው የባለስልጣኑን ዋና ዓላማዎች አደጋ ላይ የማይጥል መሆኑን ካረጋገጠ የምዝገባ መግለጫውን ማጽደቅ እንዳለበት ተመልክቷል።

የአውጪው የምዝገባ መግለጫ እንደጸደቀ ባለሥልጣኑ የተመዘገቡ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ዝርዝር፣ አይነት እና መጠን የሚያሳይ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ለአውጪው ይሰጣል። የተመዘገቡት ዋስትናዎች፣ የተመዘገበው ዓይነት እና መጠን፣ ይህ የምስክር ወረቀት የአውጪው ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች የተመዘገቡ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ መደበኛ ህጋዊ ሰነድ ነው።ይህ የምስክር ወረቀት አውጪው ሰነደ ሙዓለ ንዋዩን ለሕዝብ ለማቅረብ ወይም በሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ ለመመዝገብ ቅድመ ሁኔታ ሆኖ ያገለግላል። አውጪው በምስክር ወረቀቱ ላይ ከተመለከተው ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች አይነት እና መጠን ውጪ ለሽያጭ ማቅረብ የተከለከለ ነው።

አውጪው ሰነደ ሙዓለ ንዋዮቹን በባለሥልጣኑ ካስመዘገበ በኋላ የተመዘገቡት ነባር ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ከሆኑ በማዕከላዊ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ማከማቻ ግምጃ ቤት በማቅረብ ማስመዝገብ እና ግዑዝ አልባ ማስድረግ ያለበት ሲሆን አውጪው በበለሥልጣኑ ያስመዘገባቸው ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች አዲስ ለሽያጭ ያቀረባቸው ከሆኑ ከባለሥልጣኑ የምዝገባ ምስክር ወረቀት በተሰጠው በአምስት የሥራ ቀናት ውስጥ በግምጃ ቤቱ በማቅረብ ማስመዝገብ እና ግዑዝ አልባ ማስደረግ አለበት። አውጪው በሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ ሰነዶቹን ለማገበያየት ሰነዶቹ ቅድሚያ በግምጃ ቤቱ ማስመዝገብ ግዴታ ሲሆን እያንዳንዱን የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ባለቤቶች በግምጃ ቤቱ በማስመዝገብ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ አካውንት እንዲከፍቱ ያደርጋል።

ሌላው በባለሥልጣኑ የሚደረገው የአውጪው የምዝገባ መግለጫ የማጽደቅ ሂደት በተለያዩ ምክንያቶች ውድቅ ሊደረግ እንደሚችል ተመልክቷል። በተለይ የምዝገባ መግለጫው ያልተሟላ፣ አሳሳች፣ በማንኛውም ቁሳዊ ሁኔታ ትክክል ያልሆነ ወይም ቁሳዊ እውነታን የሚያጣ ከሆነ እና አውጪው እንደ አስፈላጊነቱ ማሻሻል ካልቻለ የምዝገባ መግለጫው ውድቅ ሊደረግ ወይም ተቀባይነት ሊያጣ ይችላል። ከዚህ በተጨማሪ አውጪው፣ ከፍተኛ ባለሙያዎቹ፣ ዳይሬክተር፣ አውጪውን የሚቆጣጠረው ሰው ወይም የውክልና ሻጩ፣ የግብይት አማካሪው ወይም የህግ ማስከበር አማካሪው በማጭበርበር፣ በእምነት ማጉደልን ወይም በተከለከሉ የግብይት ተግባራት ጥፋተኛ ሆኖ ከተገኘ ወይም መክሰሩ በፍርድ ቤት ከተረጋገጠ ምዝገባው ውድቅ ሊደረግ ወይም ተቀባይነት ላያገኝ ይችላል ። ይህ ብቻ አይደለም ደንበኛ ሳቢ መግለጫው አዋጁን፣ መመሪያውን እና የባለሥልጣኑን ትዕዛዝ የሚጥስ ከሆነም ምዝገባ ሊከለከል ይችላል።

የአውጪው ምዝገባ ከኢንቨስተሮች ጥቅም እና ከሕዝብ እምነት ጋር የሚቃረን ሲሆንም ምዝገባ ሊከለክል ይችላል። በዚህ ረገድ እንደ ምሳሌ ሊጠቀሱ የሚችሉት አቅርቦቱ ህገ-ወጥ ከሆነ፣ የሰነዱ ሽያጭ ገቢ የሚቀመጥበት የአደራ ዝግ የባንክ ሂሳብ በተፈቀደለት ባንክ ያልተከፈተ እንደሆነ፣ የአውጪው ዋና ባለድርሻዎች፣ አመራሮች ወይም ባለሙያዎች የቀድሞ ታሪካቸው ችግር ያለበት ከሆነ ምዝገባው ውድቅ ሊደረግ ይችላል።

ባለሥልጣኑ የአውጪውን የምዝገባ ጥያቄ ውድቅ ከማድረጉ በፊት የመሰማት እድል መስጠት አለበት። ባለሥልጣኑ የምዝገባ ጥያቄ ውድቅ ካደረገ ለአውጪው ውድቅ የተደረገበትን ምክንያት ተገልጾ በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት። አውጪው በዚህ ውሳኔ ላይ ቅር ከተሰኝ ይግባኙን ለኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ አስተዳደራዊ ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል።

# ሰነድ ሙዓለ ንዋይን ለህዝብ ማቅረብ

## የቁጥጥር ማዕቀፍ እና የኢንቨስተሮች ጥበቃ ዘዴዎች አጠቃላይ ትንተና

በምዝገባ ወቅት የሚቀርቡ የአውጪው መረጃዎች ለሕዝብ ይፋ መደረግ አለባቸው። ይህ ሲደረግ ተገቢው የዳታ ጥበቃ ህግ ባከበረ መልኩ እና የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ባለቤቶች የግል መረጃዎች በግል መረጃ ጥበቃ መስፈርቶች መሰረት መሆን አለበት። በዚህ መሰረት የግል መረጃዎች ተጠብቀው የአውጪው የደንበኛ ሳቢ መግለጫ ለህዝብ ይፋ የሚደረግበት አሰራር ተቀምጧል። በዚህ ረገድ የአውጪውን የምዝገባ መግለጫዎ እንደ ሚስጥራዊ ሰነድ አድርገው መያዝ አይቻልም።

አውጪው የደንበኛ ሳቢ መግለጫ ከማውጣቱ በፊት የባለስልጣኑን ፈቃድ ማግኘት አለበት። በተጨማሪም የደንበኛ ሳቢ መግለጫው ከጸደቀ በኋላ ባሉት በሰላሳ ቀናት ውስጥ ወይም ሰነደ ሙዓለ ንዋዩን ለሕዝብ ከማቅረቡ ቢያንስ ከአስር ቀናት በፊት የደንበኛ ሳቢ መግለጫውን አሳትሞ ማውጣት ወይም ለሕዝብ ተደራሽ በሆነ መልኩ ማውጣት አለበት።

በተለይ አውጪው የጸደቀውን ደንበኛ ሳቢ መግለጫ በራሱ ድህረገጽ ላይ በኤሌክትሮኒክ መልክ በማተም ለሕዝብ ተደራሽ ማድረግ ይጠበቅበታል። በተጨማሪ በባለሥልጣኑ፣ የአውጪውን ሰነድ በሚያገበያዩ የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪዎች እና የአውጪው ሰነድ በሚገበያይበት የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ ድህር-ገጽ ምዝገባውን በተመለከተ እንዲያሳውቁ መመሪያው ያዛል።

በባለሥልጣኑ የጸደቀው የደንበኛ ሳቢ መግለጫ ቢያንስ ለአስር ዓመታት በአውጪው ድህረገጽ ላይ መቀመጥ ያለበት ሲሆን አውጪው የተመዘገበውን የደንበኛ ሳቢ መግለጫ በሰላሳ ቀናት ውስጥ ለህዝብ ይፋ ሳያወጣ ቀኑ ካለፈ መግለጫው ድጋሚ ለባለሥልጣኑ ቀርቦ እንዲታይ እና እንዲገመገም ሊገደድ እንደሚችል እና ባለሥልጣኑም አውጪውን ለዚህ ስራ ተጨማሪ ክፍያዎችን እንዲፈጸም ሊያደረግ እንደሚችል ተመልክቷል።

ይህ አካሄድ ጥብቅ፣ ግልጽ እና በቴክኖሎጂ የተደገፈ የደንበኛ ሳቢ መግለጫ የማውጣት (የህትመት) ስርዓት ይፈጥራል። አውጪው ሰነደ ሙዓለ ንዋዮቹ ለሕዝብ ማቅረብ ከመጀመሩ ቢያንስ ከአስር ቀናት በፊት ደንበኛ ሳቢ መግለጫውን ለሕዝብ ይፋ ማድረግ አለበት ሲባል ሰነዱን ለመግዛት ወይም ለመሸጥ የሚፈልጉ ኢንቨስተሮች መረጃውን ለማንበብ እና ለማጤን በቂ ጊዜ እንዲኖራቸው ለማስቻል ነው።

በቀጣይ ጽሁፎች ቀሪ የሰነድ ሙዓለ ንዋይን ለህዝብ የማቅረብ እና የግብይት መመሪያ ክፍሎች ዳሰሳ በስፋት እና በጥልቀት የምንቀጥልበት ይሆናል።

የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ አስተዳደራዊ ፍርድ ቤት
Ethiopian Capital Market Administrative Tribunal
ECMAT